**<u>እሳት ድንቁም ” የኢትዮጵያ ሕዝብ ዓይንና ጆሮ</u> ”**

የብዙሃን መገናኛ አውታሮች ሬዲዮ ፣ ቴሌቪዥን ፣ ጋዜጣ ፣ ፊልም፣ ቪዲዮ ፣ እንተርኔት፣ ሞባይል ስልክ ፣ ሙዚቃ ፣ መጽሐፍ ፣ መጽሔት ፣ሌሎችንም የሚጨምር ሆኖ ብዙ ሰዎችን እንደአዘጋጆቹና አቅራቢዎቹ ዓይነት በበጎ ወይንም በመጥፎ የሚደርስና በአገርና በሕዝብ ላይ ከፍተኛ እድገት ወይንም ተፅእኖ የሚያደርሱ የግንኙነት መሳሪያዎች ናቸው ። ለሕዝብ የመረጃ ምንጭ በመሆንም ያገለግላሉ ። በአግባቡ በሥራ ላይ ከዋሉ አስተውጽአቸው ከፍተኛ ነው ። በህግና በደንብም የሚመሩ ናቸው። ሙያውም የሰለጠኑ ባለሙያዎችን የሚፈልግ ከመሆኑም ሌላ ኃላፊነትና ተጠያቂነት ያለበት ነው ። ለምሳሌ በአንድ ኮሌጅ ውስጥ የኬምስትሪ መጽሐፍና አንድ ሰነፍ መምህር ብንወስድ ፦መጽሐፉ ውስጥ ያሉት ፍሬ ሀሳቦች በመጀመሪያ ደረጃ በባለሙያ ሰዎች በግልም ይሁን በጋራ እንዲጠቀሙበት ታስቦ የታዘጋጁ ናቸው ። መምህሩ ሳይዘጋጅበት እውነታውን አጣሞ ( factual error) ለተማሪዎች ቢያቀርብ የሚከሰተው ችግር ለአገር የሚተርፍ ነው። በትምህርት አስተዳደር በኩልም በመምህሩ ላይ ከፍተኛ ቅጣት የሚያስከትል ይሆናል ። ተማሪዎችን ትክክል ያልሆነ ትምህርት ሰጥቶ የእውቀቱ ተጠቃሚ ለሚሆነው ሕዝብና አገር ሙያና እውቀት የሌላቸው ዜጎች እንዲዘጋጁ በማድረጉ ። በዚህ አጭር ምሳሌ ለመግለጽ የተፈለገው ሁሉም የብዙኃን መገነኛ አውታሮች እውነት ላይ ተመስርተው፣ በሙያው ብቃት ታንጸው ፣ ለሕዝብ አገልግሎት መስጠት እንዳለባቸው ለማሳሳብ ነው ። ሁሉም የብዙሃን መገነኛ አውታሮች ራሳቸውን የቻሉ ሳይንስም ናቸው ። ሳይንስ ደግሞ መሰረቱ እውነት ነው ። በሳይንሳዊ ዘዴና ቴክኖሎጂውን በመጠቀም መረጃ ( Information) ለሕዝብ የሚያስተላልፉ ናቸው ። ያ ካልሆነ ግን የሚያስከቱሉት ችግር በቀላሉ የሚገመት አይሆንም። ሕዝብን ውዥንብር ውስጥ ይከታሉ ።አቅጣጫንም ያስታሉ ። በመሆኑም በዘርፉ የተሰማሩት በሙሉ በከፍተኛ ጥንቃቄ መስራታቸውን መቆጣጠር አለባቸው ። አምባገነን ሥርዓቶች ባሉበት አገር እንዚህ የሙያ ዘርፎችና ባለሙያዎቹ ችግር ላይ ሲወድቁ ይታያሉ ፤ አምባገነኖቹ እውነተኛ መረጃ ለሕዝብ እንዲደርስ ስለማይፈልጉ ።

በዚህ ረገድ በአገራችን የአጼ ኃይለስላሴ፣ የፋሺስት መንግስቱ ኃይለማሪያምና የጠበቡና የዘረኛው መለስ ዜናዊ ሥርዓቶች ወቅት አገልግሎት ላይ የነበሩትንና አሁንም ያሉት የብዙሃን መገነኛ አውታሮች አድስ ዘመን ጋዜጣን፣ የኢትዮጵያ ሬዲዮን ፣ ቴሌቪዥንና ሌሎችንም የተጠቀሙትና እየተጠቀሙ ያሉት በሕዝብ ስም እየማሉ ሕዝብን ለመበደልና ለመጨቆን መሳሪያ በማድረግ ነው ። አምባገነኖችም በመሆናቸው የሚጠየቁ አልነበሩም ። የተለየ ሀሳብ ይዘው ለሕዝብ እውነተኛ መረጃ ለማቅረብ የሞከሩትን ገድለዋል ፣ አስረዋል፣ ቀጥተዋል፣ አገር ለቀው እንዲሰደዱ አድርገዋል፣ ሌሎች በደሎችንም ፈጽመዋል። ከሕዝብ ጠላቶች የሚጠበቅ ተግባርም ነበረ ። አሁንም ነው ። ወያኔ በትምህርቱ ዘርፍ የፈጸመው ወንጀል እንዲሁም በሌሎች የመረጃ ምንጮች ላይ የሚፈጽመው ደበ ሕዝብን እውነተኛ መረጃ ወይም እውቀት አሳጥቶ በአፈና ልገዛና በአጠቃለይም አገርንና ሕዝብን ለማጉዳት ነው።

ይህን ጽሁፍ እንድጭር ምክንያት የሆነኝ ራሱን ” ነጻ ሚዲያ” ና “የኢትዮጵያ ሕዝብ ዓይንና ጆሮ “ ነኝ ብሎ በመሰየም በውጭ አገር በመንቀሳቀስ ላይ የሚገኘው የኢትዮጵያ ሳተላይት ቴሌቪዥንና ሬዲዮ ጣቢያዎች የሚፈጽሙት ተግባር ነው ። ስላስቆጣኝም ንዴቴን ለመግለጽ ፈልጌ ነው ። እሳት ታሕሣሥ 2 ቀን 2006 ዓ.ም(December 11, 2013) በሬዲዮ ጣቢያው ፋሽስቱን መንግሥቱ ኃይለማሪያምን ቃለ መጠይቅ አድርጓል ። ይህን ድርጊት እሳት ያደርጋል ብዬ የጠበቅቱት አልነበረም ። በመሆኑም ልቤ አዘነ። ይህችንም ጽሑፍ ለመጻፍ ተገደድኩ ። በመንግሥቱ ኃይለማሪያም ስቃይ ደርሶብኛል ። ብዙ ወገኖቼንም አጥቻለሁ ። ፋሽስቱን ነፍሳ ገዳይ እሳት “የቀድሞው የኢትዮጵያ ፕሬዝዳንት” በማለት አስታወወቀ። መንግስቱ ኃይለማሪያም

- በአጼ ኃይለሥላሤ ዘመን ስልጣን ላይ የነበሩትንና አራት የኢሕአፓ አባሎችን ጨምሮ 60 ኢትዮጵያውያንን ያለፍርድ የገደለ መሆኑን፣
- አገሪቱ ያፈራቻቸውን የጦር መሪ ጀኔራሎችን በመግደል የኢትዮጵያ ጦርን ያለ መሪ በማስቀረት ሻእቢያ እና ወያኔ በጦር ሜዳ ፍልሚያ የበላይነት እንዲያገኙ ማድረጉን፣
- በቅርቡ በዝምባቡዌ የሚገኘው የአሜሪካ ኤምባሲ እንደገለጸው የአሜሪካንን ትእዛዝ በመቀበል በዚያ ቀውጢ ወቅት ሕዝብን ያለ መሪ ማስቀረቱን ፣ ከምእራባዉያን ሶስት ሚሊዮን ዶላር ተቀብሎ አገሪቱን የኢትዮጵያ ጠላቶች ለሆኑት ለሻእቢያ፣ ለወያኔ ፣ ለኦነግና ለሌሎችም የውጭና የአገር ውስጥ ጠላቶች አስረክቦ በመሸሸ ኢትዮጵያ አሁን ላላችበት ሁኒታ ያደረሰ ከሀዲ መሆኑን፣

- በኢትዮጵያ ውስጥ የሥልጣን ምንጭና ባለቤት የኢትዮጵያ ሕዝብ ይሁን፣ መሬት ላራሹ ይሰጥ ፣ የዴሞክራሲያዊና የሰብአዊ መብቶች ያለምንም ቅድሚያ ሁኔታ ይከበር ፣ የሴቶች የእኩልነት መብት ይረጋገጥ ፣ የብሔር-ብሔረሰቦች የእኩልነት መብት ይስፈን ፣ የሕግ የበላይነት ይከበር ፣ ደርግ ሥልጣኑን ለሕዝብ አስረክቦ ወደ ምሽጉ ይመለስ --- ወዘተ በማለት በኢሕአፓ ዙሪያና ኢሕአፓን ደግፈው ከቆሙት ብዙኃንና ሲቢል ድርጅቶች እንዲሁም ከደጋፊው ሕዝብ ወደ 500, 000 በላይ ታጋይ የሕዝብ ወገኖችን በነጻ እርምጃና በቀይ ሽብር ያስፈጃ አራመኔ መሆኑን፣
- እህትና ወንድም ገሎ ያንዱን አስካሬን በሌላው ላይ ደርቦ አባቶችንና እናቶችን ደስ ብሎናል ብላችሁ ጨፍሩ ያለ መሆኑን፣
- ታጋዮችን ገሎ አስካሬናቸውን ቀኑን ሙሉ መንገድ ላይ የጣላ መሆኑን፣
- ንጹሃን የሕዝብ ልጆችን ገሎ ቤተሰቦቻቸውን ልጆቻቸው የተገደሉበት የጥይት ዋጋ ክፈሉ ማለቱን፣
- በእስር የሚገኙ ታጋይ ልጆቻቸውን በግፍ ከማሳቃየት ሌላ ብልት ቆርጦና ከትፎ እናቶችን በማስገደድ ያበላ መሆኑን፣በዚህም ምክንያት ብዙ እናቶች ራሳቸውን እንዲያጠፉ ፣ በህይወት የቆዩትም እንዲያብዱ ያደረገ የ21ኛ ክፍለ ጫካኝ አራመኔ መሆኑን፣
- የሰውን አካል በፉላ ዘይት ያቃጠለ፣ የኢሌትርክ ኃይል በሚተላለፍበት ሽቦ የእስረኞችን ገላ የጠበሳ መሆኑን፣
- እስረኞች እጆቻቸውና እግሮቻቸው ታስሮ ሰውነታቸውን ጋዜጣን በእሳት አቃጥሎ በእሳቱ የለበለበ መሆኑን፣
- የእስረኞችን ጥፍርና አፍንጫ በጉጠት የነቀለ መሆኑን፣
- እስረኞችን ያለፍርድ ትእዛዝ ገድሎ በአንድ ጉድጓድ ከ25 በላይ አስካሬኖችን የጨመረ ከመሆኑም በላይ በአግባቡ አፈር ባለመመለሱ የጅብ እራት ያደረጋቸው መሆኑን፣
- በወንድ እስረኞች ብልት በውሃ የተሞሉ ጠርሙሶችን በማንጠልጠል መኻን እንዲሆኑ ያደረገ መሆኑን፣
- የሴቶችን ጡት የቆረጠ መሆኑን፣
- በሴቶች ብልት የብርጭቆ ጠርሙስ የሰበረ መሆኑን፣
- ወያኔ አሁን ንብቱን አይታችሁ እኔን ካልመረጣችሁ እንደሚለው ሁሉ ዝሆን ላይ ብቻ የምርጫ ካርዳችሁን ማስገባት አለባችሁ አለበለዚያ ወዮላቸው በማለት ሕገወጥ በሆነ መንገድ የተመረጠ አምባገነንና የዴሞክራሲ ጠላት መሆኑን እሳቶች በውነት አታውቁም?

መንግሥቱ ኃይለማሪያምና ሥርዓቱ የሚታወቁት ከላይ በጥቂቱ በገለጽኩበት አገራዊ ወንጀሎች ነው። የንጹሃን ኢትጵያዉያን ደም ይጮሃል። እሳት የእኛ ዓይንና ጆሮ እንዴት ይህን ከላይ የተጠቀሱትን አገርና ሕዝብ ላይ የተፈጸመውን ወንጀል ፣ግፍና በደል ማየትና ማዳመጥ አቃታችው? የወንጀሉ ዋና ተዋናይ መንግስቱን ወደ ተበደለው የኢትዮጵያ ሕዝብ በቃለ መጠይቅ ሰበብ ለማምጣት የሞራል ብቃት እንዴት አገኛችሁ ? ለኔልሳን ማንዴላ መንግሥቱ ምስክር እንዲሆን ተብሎ ነው? የ አሳት ሚና በዚህ ጉዳይ ሆድ ሲያውቅ ዶሮ ማታ ሆነብኝ ማንን ለማታለል ነው? የዚያ የተጨፈጨፈው ትውልድ አካሎችና የተበዳዮቹ ቤተሰቦች ዛሬም በሕይወት አሉ ። ዛሬም ልጄ ይላሉ ፤ ያልቅሳሉ፤ ደጅ ደጁን ያያሉ ። የልጆቻቸው ገዳይ ማን እንደሆነ ያውቃሉ። አዲሱን ትውልድ ከመንግሥቱ ጋር ለማስታዋወቅ ተፈልጎ ከሆነ ተሳስታችኋል ። ሂትለርና ሞሶሎኒ በፈጸሙት ወንጀል በበደሉት ሕዝብ ፊት ዋጋቸውን አግኝተዋል ።ታሪካቸውም መጥፎ ነው ። ትውልድም የሚያስታውሰው ከፈጸሙት መጥፎ ድርጊት አንጻር ነው ። ለመከተል የሚፈልጉ እንኳን ቢኖሩ በምን ሀቅ ያነሳሉ ? የግፉ መዘዝም ጠልፎ ይጥላቸዋል። እሳቶች የእናንተው መንግሥቱ ኃይለማሪያም ከሰዉ ተለይቶ በቁሙ የሞተ በእጁ የአገር ወደድ ኢትዮጵያውያን ደም ያለበት ነው። የእኛው ሂትለርና ሞሶሎኒ ነው። ለፍርድ መቅረብ የሚገባው ወንጀለኛ ነው። ወጣቱ ትውልድ ይህን ያውቃል። ይማራልም። ውኽንብሩ ይቁም። ለእውነት ተገዙ። ለመሆኑ የናዚ ወንጀለኞች በተገኙበት ቦታ ተይዘው ለፍርድ እንዲቀርቡ ሲደረጉ ነው እንጂ ያየናውና የሰማነው የትኛው የዓለም ሚዲያ ነው ቃለመጠይቅ ሲያደርጉ የተደመጠው። እናንተ የእኛው "ነጻ ሚዲያዎች" በየትኛው ሕግ ነው የቀይ ሽብር ወንጀል ዋና ተፈላጊና ጥቁሩን ሂትለር ቃለመጠይቅ የምታደርጉት?

እሳት ቀልዱ ቢቆም ጥሩ ነው። በቁስል ላይ ጨው ባትጨምሩ ይሻላል። ኢትዮጵያን ስንት ጊዜ የሞተለት ቀርቶ የገደላት ይበላል? ኔልሳን ማንዴላ ከእስር በተፈቱበት ወቅት የአፍሪካ ብሔራዊ ኮንግረስ ( African National Congress) ከታሰሩት ሌላ አመራር የነበረውና ከራሺያ መንግስትም ጋር የቆየ ግንኙነት ነበራቸው። በወቅቱ የነበረውን የዓለም ሁኔታ ሊራዱ የሚችሉ ነበሩ። ኔልሳን ማንዴላም ምሁር ነበሩ ፤ 27 ዓመት ሙሉ ዝም ብለው የሚቀመጡ አይደሉም ። የዓለም ሶሻሊስት አገሮችን ሁኔታ በሚመለከትም ከድርጅታቸው አመራር ሊማሩ ይችላሉ። ከመንግሥቱ ኃይለማሪያም ትምህርት ፍለጋ ወደ ኢትዮጵያ መጡ የሚለው የፋሽስቱ የለመደበት ቅጥፋት ነው። ኢትዮጵያ አገራችን በእርግጥ ለኔልሳን ማንዴላ ባለውለታ ናት። ወታደራዊ ሥልጠና ሰጥታለች። ሌሎችንም እርዳታ አድርጋለች። ለዚህ ኩራት ይገባናል። ይህ ቅዱስ የአገሪቱ በጎ ተግባር በተለያዩ ወቅት የኢትዮጵያ መሪዎች የነበሩት አምባገነኖች በሕዝብ ላይ የፈጸሙትን በደል ለማስረሳት

የሚጠቀሙበት መሳሪያ ሊሆን አይችልም። በደቡብ አፍሪቃውያን ጥቁሮች ላይ በደል ይፈጽም የነበረውን የጥቂት ነጮች የአፓርታይድ( የዘር መድልዎ) ሥርዓት ሲቃወሙ በነበሩ የኢትዮጵያ ተማሪዎችና ተራማጆች ላይ የአጼው ሥርዓትም ጥሩ አምለካከት አልነበረውም ። ደርግና ተከታዮቹም ያጠቁት በዓለም አቀፍ ደረጃ ከደቡብ አፍሪቃ የአፓርታይድ ሥርዓት እንዲወገድ ፣ ኔልሳን ማንዴላ ከእስር እንዲፈቱ ስጠይቅ የነበረውን ኢሕአፓን ፣ ደጋፊዎቹንና ሌሎች ተራማጅ ድርጅቶችን ነበሩ። ያ ከአገሩ አልፎ ለዓለም ነጻነት ፈላጊ ሕዝቦች በጎ ራእይና አመለካከት የነበረው ትውልድ እሳቶች በእናንተው " የቀድሞ የኢትዮጵያ ፕሬዝዳንት" በአምባገነኑ ኮሎኔል መንግሥቱ ተመተረ፤ ተመታ። ለአውነት የማቆም ብቃቱ ካላችሁ መንግሥቱና ማንም ገንዘብ የሰጠ ሁሉ የማይገዛችሁ ከሆነ መግንሥቱ ኃለማሪያምን የሕዝብ ጠላት ነው ልትሉ ይገባችኋል ። ለፍርድ እንዲቀርብ መጠየቅም አለባችሁ። ግን ግን ለምን በዚያ ቀውጢ ወቅት ኢትዮጵያን ጥሎ ወደ ዝምባቡዌ እንደፈረጠጠ? ያን ሁሉ ሕዝብ ለምን እንደጨፈጨፈ የመጠየቅ ብቃት አጣችሁ? በጣም የሚያዝን ፣ የሚያስቆጭ ፣ የእናንተን የነጻ ጋዜጣኝነት ሙያችሁንም ጥያቄ ውስጥ የከተተ ድርጊት ነው። ልታፍሩ ይገባችኋል። ድርጊቱም ማንንነታችሁን ግልጽ አድርጎ ያሳያ የሙያ ብቃት ጉድለት ነው ። ከሐቅ ጋር መጋጨት ነው ። በመሆኑም እሳት "የኢትዮጵያ ሕዝብ ዓይንና ጆሮ ነው " የምትሉት ውሸት ከመሆኑም ሌላ ድላለ ነው ።

በነጻ ሚዲያ ስም የኢትዮጵያን ጠላቶችን ሁሉ እሳቶች ስታስተናግዱ በማየትም ታዝብኳቸው። ኢትዮጵያንና ሕዝቧን ችግር ውስጥ እንዲጥሉ ታሪካዊ የውጭ ጠላቶቻችን ያዘጋጇት ሻእቢያን ( የኤርትራ ነጻነት ግንባር)፣ ወያኔን( የትግራይ ነጻነት ድርጅት)፣ ኦነግን(ኦሮሞ ነጻነት ግንባር)፣ ኦብነግንና ( ኦጋዴን ብሔራዊ ነጻነት ግንባር) ሌሎችንም ነው ። የእናንተ ፍቅር ግን ከእነሱ ጋር ነው። ለምን ቢባል ሕዝብ ጠላቱን ለይቶ እንዳይታገል በማድረግ ውዥንብር ውስጥ ለመክተት ነው ። "ነጻ ሚዲያ ነን" በሕዝብ የሚተዳደር እያላችሁ ከሕዝብ ገንዘብ እየሰበሰባችሁ ባላችሁበት ወቅት የግንቦት 7 ድርጅት ሊቀመንበር በውጭ ጠላቶቻችን በኩል የተላካውን $500, 000 በሻእቢያ በኩል እንደደራሳቸውና ከዚያም ውስጥ $200,000 ለእሳት ሲመድቡ በቪዲዮ የተቀረጸውን ሰምተናል። ታዲያ በምን ጥበብ ነው ራሳቸሁን ነጻ ሚዲያ ነን ፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ ዓይንና ጆሮ ነን የምትችሉት? ዓይናችሁን ጨፍኑ እናሞኛችሁ ነው የምትሉን ።እና ስብሃት ነጋ የወያኔ ድርጅት አባል የኢትዮጵያ ጠላት ነው ፣ በደርግና በኢሰፓ ውስጥ ከፍተኛ አመራር የነበሩት እና ካሳ ከበደ የእናንት ደንበኞች ናቸው ያጣፉትን ወንጀል በመጠየቅ እንዲጋለጡና ከሕዝብ እንዲገለሉ በማድረግ ፋንታ ዝም ብላችሁ አድበስብሳችሁ ታልፋላችሁ ። ይህም በእናንተ ላይ ያለኝ ሌላ ትዝብት ነው ። ወያኔ ፍርድ በኢትዮጵያ ጉዳይ በማንም ላይ ለመስጠት የሞራል ብቃቱ የሌለው መሆኑ ይታወቃል ። ወያኔ እንኳን በአምባገነኑ ኮሎኔል መንሥቱ ላይ የሞት ፍርድ በይኗል ። እሳት ግን መንግሥቱ በሕዝብ ላይ የፈጸመውን በደል መጠየቅ ሲገባው የቀድሞው የኢትዮጵያ ፕሬዝዳንት በማለት ለአምባገነኑ የማይገባውን ክብር ሰጠ ።

ቃለመጠይቅ ያዳረጋችሁት ብዙዎቹ የውጭ አገር ሰዎች ኢትዮጵያ ላይ ወንጀል የፈጸሙ ናቸው ። ግንኙነታችሁ በምን ላይ የተመሰረተ ነው? ከአገር በቀል የኢትዮጵያ ጠላቶች ጋር እንደሚታደርጉት ግንኙነት ዓይነት መሆኑ ነው? ይህም በእናንተ ላይ እምነት እንዲያጣ ያደረገኝ ሌላው ጉዳይ ነው። ስለዚህ እሳት ራሱን "የኢትዮጵያ ሕዝብ ዓይንና ጆሮ " ብሎ መሰየሙን ድንቄም ልለው ተገደድኩ። ተራ ማታለያ መሆኑንም ተገናዘብኩ ። "ነጻ ሚዲያ " የምትሉትንም እንደዚሁ።

ለማጠቃለል የሚዲያ ሥራ እውቀትን የሚጠይቅ፣ እውነትን መሰረት የሚያደርግ ፣ ግልጽነት ያለው ፣ ኃላፊነትና ተጠየቂነት ያለበት የሙያ ዘርፍ ነው። በመጠራራት፣ በዝምድናና ጥቅምን ቅድሚያ በመስጠት የሚከናወን ተግባር አይደለም ። የአገርንና የሕዝብን ጥቅም የሚያስቀድም ሙያ ነው። እሳት ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጠላቶች ጋር የምታደርጉት ግንኙነት አገርን ፣ ሕዝብንና ትግልን የሚጎዳ ስለሆነ ቆም ብላችሁ አካሄዳችሁን መርምሩ ። ከመንግሥቱ ኃይለማሪያም ጋር ላዳረጋችሁት ግንኙነትም የኢትዮጵያን ሕዝብ ይቅርታ ጠይቁ። ለመታረም ብቃቱና ፍላጎቱ ካላችሁ። እየተጋለጣችሁ መሆኑንም ተገንዘቡ። ለዴሞክራሲ፣ ለሰው ልጅ መብትና እኩልነት የሚቆረቆሩ ኢትዮጵያውያን ሁሉ እሳት በነጻ ሚዲያ ስም መንግሥቱ ኃይለማሪያምንና ሌሎችንም የአገርና የሕዝብ ጠላቶችን እያስተናገደ ስለሆነ ለፈጸመው ጥፋት ይቅርታ ሕዝቡን እስከሚጠየቅና ጠላትና ወዳጅን ያልለየ ድርጊቱን እስከሚያቆም ድረስ እንድትቃወሙና የምትሰጡትን ሁሉንም ድጋፍ እንድትታቋርጡ እጠይቃለሁ ።

ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኖራለች !!

ጠላቶቿ ሁሉ ይወደሙ !!

እሳት በነጻ ሚዲያ ስም ማጭበርበሩን አቁም !!

በረከት ሳሙኤል( ኢትዮጵያ)